# ትምህርት ሰጭ የኢትዮጵያ ሜድያዎች ስብሰባ። ከእሸቴ ውለታው

ዘንድሮ ለ32ኛ ጊዜ በሰሜን አሜሪካ የስፖርት ፌዴሬሽን የተዘጋጀው የእግር ኳስ ጨዋታ በሜሪላንድ ግዛት ዋሽግተን ነበር ሜሪላንድ በውብ ኢትዩጵያውያን አምራና ተውባ ነበር የከረመች።

የዘንድሮ እግር ኳስ ዝግጅት እንደወትሮው ነገር ግን በጣም ባማረና በደመቀ ሁኔታ የእግር ኮስ ጨዋታው ፣ የንግድ ልውውጡ፣ባህላዊናዘመናዊ የሙዚቃ ፊስትባሉ ፣ኢትዩጵያን መሰረት ያደረገ ፓለቲካ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች ወዘተ የተከናወነበት ነው።

በሁሉም ክንውኖች አቅሚ እንደፈቀደ ተሳታፊና ታዳሚ ሁኛለሁ ከሁሉ በላይ አቅሌን የሳበኝና የማረከኝ በአዲስ ድምፅ ራዲዩ በአበበ በለው አዘጋጅነት የነበረው የጋዜጠኞችና የሜዴያ አዘጆች ሚና በኢትዩጵያ የዲሞክራሲና የነፃነት ትግል ምን መሆን አለበት? በሚል የመወያያ ርእስ የቀረበው ውይይት እጅግ አስተማሪና ሚዲያዎች ያለባቸውን ችግር በግልፅ የተነጋገሩበት በመሆኑ በአይነቱ የተለየ ነበር።

በዚህ ስብሰባ በፓናል የውይይት አቅራቢ የነበሩት ታዋቂው፣ አንጋፋው ኢኮኖሚስትና አክትቪስት ዶ/ር አክሎክ ቢራራ ፣ የዞን ዘጠኝ ጦማሪ ሶሊያና ሽመልስ፣የኢትዩጵያ ሪቪው አዘጋጅ ኢልያስ ክፍሌ፣የኢትዩጵያ ሜዲያ ፎረም (EMF) አዘጋጅ ክንፉ አሰፋ፣በቴሌ ታዋቂው አክትቪስት አበበ ገላውና የአዲስ ድምፅ አዘጋጅ አበበ በለው በየተራ ርእሱን መሰረት በማድረግ በሳልና ጠቃሚ ንግግር አድርገዋል።

የስብሰባው መሪ አቶ ዳዊት ተገኘ በመጀመሪያ ንግግራቸው ባለፈው ሀያ አራት ዓመት አምባገነኑን የወያኔን ኢህአደግ አስተዳደር በህዝባችን ላይ የሚደርሰውን ኢሰብአዊ የሆነ ጭፍጨፋና ግድያ፣ ህዝባችንን በዘርና በኃይማኖት በመከፋፈል ማቆሚያ የለለው እልቂትና ፍጅት በመፍጠር
የሚሰራቸን ሴራና ደባዎችን በማጋለጥና መረጃ በመስጠት፣በተለይ በምርጫ 97 ኢትዩጵውያን ጋዜጠኞች የሰሩት ስራናያደረጉት አስተዋፅኦ በታሪክ የሚረሳ አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ ይህን ሥርአት ፊት ለፊት የታገሉትና እርቃነን ሥጋውን በማጋለጥ ለኢትዩጵያ ህዝብና ለዓለም ህብረሰብ ያሳወቁት ኢትዩጵያውያን ጋዜጠኞችና የሜዴያ ሰዎች ናቸው። በውጭም ማለት በዲያስፓራው ህዝቡን በማነቃነቅና በማደራጀት መረጃ በመስጠት፣ ትግሉና ምርጫ ለውጤት እንዲደርስ ከማንም በላይ ከፊት ሁነው የሰሩት በውጭ አገር ያሉ ጋዜጠኞች ና የሚድያ ሰዎች ናቸው። ለአብነት ያህል ከመሀላችን ካሉት የኢትዩጵያ ሪቪው አዘጋጅ ኢልያስ ክፍሌ፣ የኢምኤፍ (EMF) አዘጋጅ ክንፉ አሰፋ፣የአዲስ ድምፅ አዘጋጅ አበበ በለው እነዚህ ወንድሞች በምርጫ 97 በተደረገው ትግልና ለቀጣዩ የዲሞክራሲ ና የነፃነት ትግል መሪ ተዋናይና ግንባር ቀደም አንቂና አስተባባሪዎች ናቸው ለእዚህ ነው አምባገነኑ የወያኔ ሥርዐት በለሉበት የረጅም አመት እድሜ የፈረደባቸው

ዘረኛውን የወያኔ ከፋፋይና ፀረ ዲሞክራሲና አፋኝ ሥርዐት በሰላ ብእራቸው በማጋለጣቸውና በመታገላቸው በአምባገነኑ ሥርአት ሰለባ ሁነው በመከራ ቤት በእስር የሚገኙትን እነ እስክድር ነጋን፣ርእዩት አለሙ፣እነ ተመስገንን፣እነ ውብሸትን ወዘተ ስናስታውስ እና ለዲሞክራሲና ለነፃነት በመናገራቸው ና በመፃፋቸው ከግፈኛው ስርአት ደህንነቶች አምልጠው የሚወዷቸውን ልጆቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ተለይተው ሳድይወድ በግድ ተሰደው በባእድ ሀገር በአፍሪካና በመካከለኛ አረብ በስደትና በመከራ ያሉት ስናስውስ የኢትዩጵያ ጋዜጠኞችና የሚድያ ሰዎች ይህን ሥርአት ምን ያህል እንደታገሉትና ዋጋ እንደከፈሉበት የሚሳይ ነው።

አቶ ዳዊት ንግግሩን በመቀጠል
በእስር፣ በግዞትና በስደት የሚገኙ ጋዜጠኞች መስዋአትነት የሚስተምረን ሁለት አደራ አለ። አንደኛው ለማይቀረው የነፃነት ትግል በርትተንናተጠናክረን እንድንታገል።ሁለተኛው ኢትዩጵውያን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ሊኖራቸው ስለሚገባ
የዲሞክራሲ መብት ማለት የመናገር፣የመፃፍ፣የመደገፍ፣ የመቃወምና የመተቸት ወዘተ
እስቴችን እንደ ሰው ልጅ ማግኘት
ማስከበርና ለዚህ የዲሞክራሲ መብትና ነፃነት በየትኛው ደረጃና በየትኛውም ቦታ መታገል እንዳለብን
በእነርሱ መስዋእትነት አስተምረውናል አደራብለውናል ከዚህ አንፃር እናንት
በውጭ ማለት በዲያስፖራ የምትገኙ
ጋዜጠኞች ና የሜዴያ ሰዎች ምን ያህል ነፃ ናችሁ? ለህዝብ የምታቀርቡት ዘገባና ዜና ምን ያህል ከቀረቤታና ከፓለቲካ ድርጅት አፍቃሪነት ገለልተኛ ነው? የፓለቲካ ድርጅቶች ገለልተኛና ነፃ ሜዲያ መሆናችሁን አምነው ምን ያህል መብቶቻችሁን ያከብራሉ? የመሳሰሉት ጥያቄዎች በማቅረብ ለስብሰባው ታዳሚ ውይይቱን ክፍት አድርገውታል።
በቤቱ ተመሳሳይ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ቀርበዋል አብዛኛውን ከቀረቡት አስተያያቶች በአብዛኛው
ያነጣጠረው የግለሰቦችን የመናገርና የመተቸት መብት እተጋፋ
ያለው ግንቦት ሰባት በሀገራችን ጉዳይ በተለይ ኤርትራና ሻቢያ በተመለከተ የሚደረጉትን ውይይቶች
ህዝብ እንዳይወያይበትና አስተያየት
እንዳይሰጥበት የሚደርገው የጉልቤና የአፈና አካሄድ መቆም አለበት በሀያ አራት አመት ትግል ፀንተው በፀረ ወያኔና ሻቢያ

አቆም ታግለው ያታገሉ ወንድሞችን ስለ ሻቢያና ኢሳያስ አፈወርቂ አነሳችሁ በሚል እናንት የወያኔ ተላላኪዎች ተብለው እየተሰደቡ ነው።ይህን አካሄድም ትክክል አለመሆኑና ለማስቆም የድርጅቱ መሪዎች ያደረጉት ጥረት የለም ይልቁንም የድርጅቱ መሰረታዊ ፍልስፍና ስድብ፣ጭሆትና አድማ እስኪመስል ድረስ ቀጥለውበታል
ታዳሜው ይህን አካሄድ ከምንትልገለው የወያኔ ሥርአት ተለይቶ ስለማይታይ አካሄድን እንታገለዋለን በተረፈ ትናንት በኢትዩጵያ ሪቪው አዘጋጅ በኢልያስ ክፍሌ ዛሪ በአዲስ ድምፅ አዘጋጅ በአበበ በለው እየተደረገና በመደረግ ላይ ያለው ጋጠ ወጥ ዘመቻ የተሰለፍበትን ድርጅት ሰብእና የሚሳይ ስለሆነ ሊታረም ይገባል። ኢልያስ ክፍሌ ሆነ አበበ በለውን ወያኔ ለማለት ቀርቶ ደጋፊዎች ሌላውም የሞራል ብቃት የላቸውም። በዚህ ጉዳይ በእጥነወት የተገለጠው ለግንቦት ሰባት ድርጅትና ለለውጥ ፈላጊው አባላት ከፍተኛ አክብሮት እንዳለው አስምሮበታል

ድርጅቶችን አንተች የሚለው አባባል ስህተትና ወቅታዊ አለመሆኑ ተተችቶበታል ወያኔ ሀያ አራት አመት በግፍና በበደል ህዝባችንን እየከፋፈለና እያሰቃየ በአምባገነንነት መግዛቱን እኛም ያለመስልቸት በፅናት ሀያ አራት ዓመት አጋልጠነዋል ነገር ግን ህዝቡን መርተውና አደራጅተው ለድል ያበቁታል ያልናቸው የፓለቲካ ድርጅቶች ህዝቡን ለድልና ለነፃነት አለማብቃት ብቻ ሳይሆን ራሳቸው ወደህብረትና አንድነት ባለመምጣት

ራሳቸውን ሊያዩና እንዲፈትሹ ጥሪ ማድረግ እኛም ሆነ ህዝቡ ልንተቻቸውና ልንገመግማቸው ይገባል ይህ አካሄድ ለድርጅቶች ና ለትግሉ ብርታትና ጥንካሪ ይሰጣቸዋል የህዝብ ትችትየሚፈራ
አምባገነን መንግስትና ራሱን በትእቢት ያሳበጠ ውስጡ በባዶ ጭሆት የሞላ ኃይል ብቻ ነው።

በመጨረሻ በፓናል አቅራቢዎችና በታዳሚው የተደረስበት መንፈስ

1ኛ/ የፓለቲካድርጅቶች፣አባሎቻቸውና
ሌላው ማህብረተስብ የነፃ ሚድያን ሚና እንዲረድልን ጥረ ማድረግ፣በሚድያ አቀራረብ በፅሁፍ ዘገባ፣ በዜና ሆነ በቃለ መጠይቅ የሚስራው ጥንቅር አቅራቢውጋዜጠኛ ህዝብ ሊውቀው
ይገባል ብሎ ያመነበትን የማቅረብ ሙሉ መብት እንዳለው። አዘጋጅው ይህን ማቅረብ የእገሊን ድርጅት ያስከፋብኛል በሚል ስነ ልቦናዊ ሰቀቀን እንዲፈጠር የሚደረገው ዘመቻ መቆም አለበት ድርጅቶች ነፃ ሚዲያዎችን የእነርሱ ልሳን እንዲሆኑ በቀጥታ ሆነ በተዘዋሪ መሞከር ወንጀል ነው።ድርጅቶች የነፃ ሚድያዎችን ሽፋን ማግኘት የሚችሉት በሚሰሩት ሥራና መሪት ላይ በተግባር በሚደርጉት አስተዋፅኦ እንጅ ሚዲያዎችንና አዘጋጆችን በማንቆሸሽ ና በማሸበር አይደለም።

2/ኛ የሜዲያ አዘጋጆች የተመክሮ ልውውጥ ማድረግ አለብን በሚል የህሊና ራዲዮ አዘጋጅ ሳምሶም ውብሸት የሙያ ትንተና ትምህርት ሰጭ በመኑነ በትክክል ከነፃ ሚድያነት አንፃር እየሰራን ስለመሆኑ ትምህርታዊ ግምገማ ለማድረግ አንድ ፎረም ማቆቆሙ ጠቃሚ በመሆኑ የአዲስ ድምፅ አዘጋጅ አበበ በለው በአስተባባሪነት ተመርጦ ሌሎች የሚዴያ ባለ ቤቶችን ጨምሮ አንድ ፎረም እንዲቆቆም ተወስኖአል።

3/ኛ በተለይ ዘ ሀበሻ አዘጋጅ ጋዜጠኛ ሄኖክ በሰጠው ማሳሰቢያ መሰረት ለሀገራቸው፣ ለህዝባቸው ነፃነት ሲሉ ሥርአቱን ተችታችሆል ህዝብን አነሳስታችሆል በሚል በእስር ና በስደት የሚገኙ የጋዜጠኛ ቤተሰቦች ልንረዳቸውና ልናበረትታቸው ይገባል።ሄኖክ በመቀጠል በትናንት ቀን እኔና የሚድያ ሰዎች እዚህ ቤት ያለን የጀግናው ጋዜጠኛ ባለቤት ወ/ሮ እስከዳርና ልጆን በማየታቸውና በመነብኘታቸው ከፍተኛ የህሊና ደስታ እንደተሰማው ገልፆ እኛ በውጭ የምንገኝ ጋዜጠኞች፣ የፓለቲካ ድርጅቶችሆነ ዲያስፖራው
እነዚህን ለህዝብ ልሳን በመሆን በወይኔ እስር ቤት ያሉ ፋኖ ቀዳጅ የሆኑ ትንና በስደት የሚገኙትን ልንረሳቸው አይገባም ስለዚህ የምንመሰርተው ፎረም በአገዛዙ እጅ የወደቁትንና ቧእድ ሀገር የተሰደድትን ጋዜጠኞችንና ቤተሰባቸውን የምረዳበት የምንደግፍበትና የምንዘክርበት መሆን አለበት ብሎል።
በአጠቃላይ ስብሰባው በጥሩ መንፈስና በበሳል አካሄድ የተካሄደ ነበር። ታዳሚው የሁሉንም ማህረሰብ አባላት ያካልተተ ሲሆን የቆየ የፓለቲካ ተመክሮ ያላቸው ፣ የፓለቲካንድፍፀሀፊዎች፣ጦማርያንና
የፓልቶከ ባለቤቶችን ያከተተ ነበር። በታዳሚነት ካየሆቸው መሀል ታዋቂው የሰብአዊ መብት ተማጎች አባንግ ሜቶና ታምረኛው ብእረኛ ተክሌ አበበ ነበሩ።